Angela D. Alsobrooks
County Executive

# UPON REQUEST

# እውነታ ወረቀት

## CB-014-2022 ምንድን ነው?

የፕሪንስ ጆርጅ ካውንቲ CB-014-2022፤ ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚያገለግሉ የምግብ ዕቃዎች መለዋወጫዎች ስርጭትን፤ እና የምግብ ተቋማትን መደበኛ ቅመሞች፤ ለደንበኞች ይቆጣጠራል።

## ይህ ህግ መቼ ተግባራዊ ይሆናል?

CB-014-2022 ሰኔ 1፣ 2023 (እ.አ.አ) ላይ ተግባራዊ ይሆናል።

## CB-014-2022 ማን ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል?

በፕሪንስ ጆርጅ ካውንቲ እና በተጠቃሚዎቹ ውስጥ የሚሰራ ማንኛውም የምግብ አገልግሎት ንግድ።

የምግብ አገልግሎት ንግድ ማለት፤ ሙሉ አገልግሎት የሚሰጡ ምግብ ቤቶች፣ ውስን አገልግሎት የሚሰጡ ምግብ ቤቶች፣ ፈጣን ምግብ ቤቶች፣ ካፌዎች፣ የስጋ ተዋጽኦ መሸጫዎች፣ የቡና መሸጫ ሱቆች፣ ሱፐርማርኬቶች፣ የምግብ መደብሮች፣ የጭነት መኪናዎች ወይም ጋሪዎች፣ የምግብ መኪናዎች፣ ካፊቴሪያዎች (በካውንቲው ወይም ካውንቲውን በመወከል የሚንቀሳቀሱትን መምሪያዎችን እና ወኪል ድርጅቶችን ጨምሮ)፣ እና ሌሎች የሽያጭ አካላት ወይም በካውንትቲው ውስጥ ወይም ውጪ የተዘጋጁ ወይም ለመበላት ዝግጁ የሆኑ የምግብ ፍጆታዎችን የሚያቀርቡ።

የሶስተኛ ወገን የምግብ ማዘዣ መድረክ ማለት፤ የተዘጋጀ ምግብ እና መጠጥ ሽያጭ የሚያቀርብ ወይም የሚያዘጋጅ፤ እንዲሁም ምግብና መጠጦችን ከምግብ አገልግሎት ንግዶች የሚያስረክብ ወይም የሚወስድ ማንኛውም ድህረ ገጽ ወይም ሌላ የበይነ መረብ አገልግሎት ነው።

## የእኔ ንግድ CB-014-2022ን ማክበር ካልቻለስ?

ህጉን የሚጥሱ የምግብ ድርጅቶች እና የሶስተኛ ወገን የምግብ ማስረከቢያ መድረኮች፤ መቀጮ ይጣልባቸዋል፡

የ1ኛ ጊዜ ጥሰቶች ማስጠንቀቂያ ይደርሳቸዋል።
የ2ኛ ጊዜ ጥሰቶች የ $250 ቅጣት ያስከትላሉ።
የ3ኛ ጊዜ ጥሰቶች የ $500 ቅጣት ያስከትላሉ።

## የ CB-014-2022 ዓላማ ምንድን ነው?

- በችርቻሮ የምግብ ኢንዱስትሪ ውስጥ ለአንድ ጊዜ ብቻ ከሚያገለግሉ ዕቃዎች የሚመነጨውን አላስፈላጊ ቆሻሻ ለመቀነስ፤
- የማህበረሰቡን አባላት ጤና እና ደህንነት ማሻሻል፤ እና
- የውሃ መስመሮች ንፁህ እና ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ለማገዝ።

## ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚያገለግሉ የምግብ ዕቃዎች መለዋ ወጫዎች ምንድን ናቸው?

ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚያገለግሉ እቃዎች፤ መምጠጫዎች፣* የኩሽና እቃዎች፣ ቅመሞች ኩባያዎች እና ማሸጊያዎች፣ የኩባያ መያዣዎች፣** መክደኛዎች፣ ማማሰያዎች እና ናፕኪንን ጨምሮ፤ ለመበላት ዝግጁ ከሆነ ምግብ ጋር የሚቀርቡ እና ለአንድ ጊዜ ለማገልገል እና ከዚያም ለመጣል የተሰሩ።

## የአገልግሎቱ መስፈርቶች ምንድን ናቸው?

**ውስጥ የመመገቢያ/የውጪ ትዕዛዞች፡**
ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚያገለግሉ የምግብ ዕቃዎች መለዋወጫዎች እና ቅመሞች፤ ደንበኞች በሚጠይቁ ጊዜ ወይም በራስ አገልግሎት በሚሰጡ ጣቢያዎች ብቻ ይሰጣሉ።

**የበይነ መረብ የማስረከቢያ ትዕዛዞች፡**
የሶስተኛ ወገን ማስረከቢያ መድረክን የሚጠቀሙ የምግብ ድርጅ ቶች፤ ደንበኞቻቸው በትዕዛዞቻቸው ሊጠይቁ የሚችሉትን የአንድ ጊዜ አገልግሎት መለዋወጫዎች/ቅመሞች ዝርዝር፤ ከሜኗቸው ጋር ማዘጋጀት አለባቸው።

## የአገልግሎቱ መስፈርቶች ምንድን ናቸው?

ካውንቲው ደንቡን ከ ጥቅምት 1፣ 2023 (እ.አ.አ) ጀምሮ ማስፈጸም ይጀምራል። ድርጅቶች ለጥያቄዎቻቸው ወይም ስጋቶቻቸው፤ **DoECares@co.pg.md.us** ን ማግኘት ይችላሉ።

*በካውንቲ ህግ መሰረት፤ ወደ ብስባሽ መቀየር የሚችል እና የወረቀት መምጠጫዎች ተፈቅደዋል።

**የመጠጫ ዕቃ መያዣዎች፤ ለንግድ ስራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይፈቀዳሉ።

Prince George's County Department of the Environment

Prince George's County, MD Proud Get to Know Us

ህጉ ምን እንደሚጠይቅ እና ለማክበር ሊወስዷቸው ስለሚችሉት እርምጃዎችን የበለጠ ለማወቅ፤
**mypgc.us/singleuse** ይጎብኙ